# ረቂቅ - 3/18/21

## የአረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ዘማቾች አገልግሎቶች ክፍል የ2021-2025 ዓ.ም የቦታ እቅድ

የአረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ዘማቾች አገልግሎቶች ክፍል (ADVSD) የ2021-2025 ዓ.ም የአረጋውያን የቦታ እቅድ ላይ የቦታ ድርጅቱን ረቂቅ ግቦችና አላማዎቹን በሚከተለው መልኩ አጠቃሎ አቅርቧል።

**ነባር የአሜሪካ ተወላጅ አረጋውያን**

1. በከተማ አካባቢዎች የሚኖሩ ነባር የአሜሪካ ተወላጅ አረጋውያንን በሚያገለግሏቸው ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች አማካኝነት ማገልገል።
    a. የነባር ተወላጅ አረጋውያን ከእንክብካቤና ደህንነት፣ እንዲሁም ከቤተሰቦቻቸው፣ ጎሳዎቻቸው እና የጎሳ ማህበረሰቦቻቸው ጋር ተያያዥ ቅደም ተከተሎች ላይ ADVSD ግንዛቤ ተወስዶባቸው ቅድሚያ ይሰጠዋል።
    b. ተጨማሪ ነባር የአሜሪካ ተወላጅ አረጋውያን በADVSD የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግባቸው ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

**ጾታ የቀየሩ እና ከሁለቱም ጾታዎች ውጭ የሆኑ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና ባለ ሁለት መንፈስ አረጋውያን**

1. ጾታ የቀየሩ እና ከሁለቱም ጾታዎች ውጭ የሆኑ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና ባለ ሁለት መንፈስ አረጋውያንን ደህንነት፣ ነጻነት እና እንደ እድሜያቸው በራስ መወሰንን ለመደገፍ የማህበረሰብ እንክብካቤ እንዲያገኙ እና አገልግሎቶችና ፕሮግራሞችን እንዲጠቀሙ ለማስቻል ከነርሱ ጋር በአግባቡ ግንኙነት ይደረጋል።
    a. የADVSDን አገልግሎቶች እና የአረጋውያን አገልግሎቶች ኔትወርክን ማግኘትና መጠቀም የሚፈልጉ ጾታ የቀየሩ እና ከሁለቱም ጾታዎች ውጭ የሆኑ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና ባለ ሁለት መንፈስ አረጋውያንን ብዛት መጨመር።

2. ጾታ የቀየሩ እና ከሁለቱም ጾታዎች ውጭ የሆኑ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና ባለ ሁለት መንፈስ አረጋውያን አገልግሎቶችን በእድሜ ለገፉ አዋቂ ሰዎችና አካል ጉዳተኛ ሰዎች ተደራሽ ለማድረግ ማህበረሰብ ተኮር አሰራርን ይመራሉ።
    a. ጾታ የቀየሩ እና ከሁለቱም ጾታዎች ውጭ የሆኑ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና ባለ ሁለት መንፈስ አረጋውያን ከቤት ውስጥና ማህበረሰብ ተኮር አገልግሎቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፍላጎቶቻቸውን ለይተው ያወጣሉ፣ ቅደም ተከተል ያስይዛሉ እንዲሁም ምክረ ሀሳቦችን ይሰጣሉ።

**መረጃና ድጋፍ (I &A) እና የአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች የመረጃ/ድጋፍ ግንኙነት (ADRC)**

1. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች፣ አካል ጉዳተኛ ሰዎች እና ተንከባካቢዎቻቸው ስለ ADRC ተገንዝበው መረጃ፣ ድጋፈፍና አገልግሎቶች እንደማግኛ መሳሪያ ይጠቀሙበታል።
    a. በአካል፣ በባህልና በቋንቋ የተገለሉ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች የሚያጋጥማቸውን መገለልና የተደራሽነት እንቅፋቶች ለመቀነስ የADRC አጠቃቀማቸውን ያሳድጋሉ።

2. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች፣ አካል ጉዳተኛ ሰዎች፣ ቤተሰቦቻቸው እና ተንከባካቢዎቻቸው በመረጃ፣ ሪፈራልና የድጋፍ ኔትወርክ አማካኝነት ከድጋፍ ምንጮችና አገልግሎቶች ጋር በአግባቡ ይገናኛሉ።
    a. የማህበረሰብ አጋሮችና በታሪክና አሰራር በተገለሉ የማህበረሰብ አባላት የማህበረሰብ ግንኙነቶች ላይ የሚሰሩ ተቋማት ስለ ADRC እና የI & A ኔትወርክ አውቀው እነዚህን ይጠቀማሉ።

**የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎቶች**

1. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች በቀላል ዋጋ የሚቀርብ፣ ለባህል አግባብነት ያለው እና ጤናቸውን የሚደግፍ ምግብ በበቂ ሁኔታ ያገኛሉ።
    a. በእድሜ ለገፉ አዋቂ ሰዎች የሚቀርቡ እንደ የተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብ ድጋፍ ፕሮግራም ወይም SNAP የመሳሰሉ በፌደራል የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግባቸው የተመጣጠነ ምግብ ፕሮግራሞች አጠቃቀማቸውን ያሳድጋሉ።
    b. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች መጠነ ሰፊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በተለያዩ ቦታዎች በአነስተኛ ወጪ ወይም ያለ ምንም ወጪ የሚቀርብ ምግብ ያገኛሉ።

2. በታሪክና አሰራር ምክንያት ለተገለሉ የማህበረሰብ አባላት ቅድሚያ በመስጠት በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና አካል ጉዳተኛ ሰዎች የምግብ ተደራሽትን ለማሳደግ በማህበረሰብ የሚመሩ ጥረቶች ይደገፋሉ።
    a. የመግብ ተደራሽነት እና የተመጣጠነ ምግብ ምንጮች ላይ በእድሜ ለገፉ በታሪክና አሰራር ምክንያት ለተገለሉ አዋቂ ሰዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

**የጤና ማስተዋወቂያ**

1. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች እና አካል ጉዳተኛ ሰዎች ለደህንነታቸው እና አካላዊና የአእምሮ ጤናቸው ድጋፍ ለማድረግ ከማህበረሰባቸው ጋር ጠንካራ ግንኙነት ይፈጥራሉ።
    a. በአጋርነትና የኔትወርክ ልማት አማካኝነት በእድሜ ለገፉ አዋቂ ሰዎች የሚቀርቡ የጤና ማስተዋወቂያ ክፍለ ጊዜዎችና ተግባሮች አቅርቦት ከፍ ይላል።

2. ስር የሰደዱ የጤና ሁኔታዎችን ለመፍታት፣ ጤናን ለማሳደግ እና መገለልን ለመቀነስ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች በጤና ማስተዋወቂያ ተግባሮች ላይ በንቃት ይሳተፋሉ።
    a. ተጨማሪ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች ጤናና ደህንነትን ለመደገፍ በሚካሄዱ ተግባሮች ላይ ይሳተፋሉ።

**የቤተሰብ ተንከባካቢዎች**

1. በታሪክና አሰራር የተነሳ ለተገለሉ ማህበረሰቦች ቅድሚያ በመስጠት የቤተሰብ ተንከባካቢ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ለቤተሰብ ተንከባካቢዎችና መደበኛ ያልሆኑ ተንከባካቢዎች ይቀርባሉ።
    a. በታሪክና አሰራር የተነሳ ለተገለሉ ማህበረሰቦች ተንከባካቢዎች የአገልግሎቶች ቅድሚያ በመስጠት የቤተሰብ ተንከባካቢዎችና መደበኛ ያልሆኑ ተንከባካቢዎች ተሳትፎ እንዲያድግ ይደረጋል።

2. የቤተሰብ ተንከባካቢዎች ግለሰብን ያማከሉና ለባህል ልዩ የሆኑ አገልግሎቶችን ያገኛሉ።
    a. ለባህል አግባብነት ያላቸውና ምላሽ ሰጪ አገልግሎቶችን የሚያገኙ የቤተሰብ ተንከባካቢዎች ብዛት እንዲጨምር ይደረጋል።

**የአረጋውያን መብቶችና የህግ ድጋፍ**

1. በታሪክና አሰራር የተነሳ የተገለሉ ማህበረሰቦች ለደራሽነትን ለማስፋት አጽንኦት በመስጠት በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች በነባሩ የሕግ ፕሮጀክት አማካኝነት የህግ ምክር ያገኛሉ።
    a. በእያንዳንዱ አመት በአማካኝ ለ900 በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች የህግ ድጋፍ ይቀርባል።
    b. በነባሩ የሕግ ፕሮጀክት አማካኝነት በታሪክና አሰራር ምክንያት ለተገለሉ አረጋውያን የሚቀርበውን አገልግሎት አቅም ማሳደግ።

2. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች ለአቻ ድጋፍና እራስን ማስተዋወቅ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ድጋፎች ያገኛሉ።
    a. አሁን ያሉትን እራስን የማስተዋወቂያ ድጋፎችና የአቻ ለአቻ ትስስሮች ማስተዋወቂያ የስምሪት ዘመቻ ይዘጋጃል።

**የመጓጓዣ አስተዳደር እና አገልግሎቶች**

1. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች ስለሚቀርቡላቸው የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፎች ይገነዘባሉ።
    a. በታሪክና አሰራር ምክንያት ለተገለሉ የማህበረሰብ አባላት ቅድሚያ በመስጠት የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፎች በእድሜ ለገፉ አዋቂ ሰዎች ይከፋፈላሉ።
    b. የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፎች በእድሜ ከገፉ አዋቂ ሰዎች የአገልግሎት ስርአት ጋር ይቀናጃሉ።

2. የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፎች ለማህበረሰብ ምርጫ ቅድሚያ ይሰጣሉ እንዲሁም የኮቪድ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን ያከብራሉ።
    a. በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎች ቀጣይነት ካለው የአገልግሎት አቅርቦት እና ከCOVID-19 ጋር ተያያዥ ፍላጎቶችና ምርጫዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የትራንስፖርት ፍላጎቶች ላይ በADVSD ግንዛቤ ተወስዶባቸው መፍትሄ ይሰጣቸዋል።